# ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ ማሳሰቢያ

**ጳጉሜ 3 ቀን 2000 ዓ.ም. ( September 8, 2008 )**

**የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ የሃገራችን ሰፊ የድንበር ውሃ-ገብ ለምና ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ያለውን መሬት የወያኔ/ኢሕአዴግ ገዥ ቡድን ለሱዳን በድብቅ አሳልፎ የመስጠቱን ሴራና ወራሪው የሱዳን ጦር የሃገራችንን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በመድፈር በወገኖቻችን ላይ ያደረሰውን ግድያ ፣ አፈና ፣ ንብረት መዝረፍና ማቃጠል በይፋ በማጋለጥ የኢትዮጵያ ሕዝብና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዓለም-አቀፍ ተቋማት እንዲያውቁት አድርገናል።**

**የሃገራችንን ዳር ድንበር የማስጠበቅ የታሪክና የዜግነት ግዴታ ስለአለብን ፤ አሁንም የድንበሩን ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ እየተከታተልን እናቀርባለን።**

**እስከአሁን ድረስ ስንጠራበት የነበረው ስማችን ማለትም « የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ( Ethiopia-Sudan Border Affairs Committee ) » ውስጥ « Sudan » የሚለው ቃል በወቅቱ በአለው ዓለም-አቀፍ ትኩረት ምክንያት የአሰራር ችግር ስለፈጠረብን ፤ የኮሚቴውን ስም ማስተካከል ተገቢ መሆኑን የድንበር ኮሚቴው ምክር ቤት አምኖበታል። በዚሁ ረገድ ያለንበት ሃገር የሚጠይቀውን አስፈላጊውን ሕጋዊ ሥርዓቶች በማሟላት በኮሚቴአችን መጠሪያ ስም ላይ መጠነኛ ለውጥ ስለአደረግን ከጳጉሜ 1 ቀን 2000 ዓ.ም. ( September 6, 2008 ) ጀምሮ « የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ( Ethiopian Border Affairs Committee ) » ተብሎ መሰየሙን በታላቅ ትህትና እናስታውቃለን።**

**ከስም ለውጡ ጋር ተያይዞ አድራሻችን ፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥራችንና ኢሜላችን ተቀይሯል። በዚሁ መሠረት ፥**

**1ኛ/ አዲሱ አድራሻችን ( Our New Address ):**
**Ethiopian Border Affairs Committee**
**P. O. Box 9536**
**Columbus, OH 43209 USA**

**2ኛ/ አዲሱ የባንክ ሂሳብ ቁጥራችን ( Our New Bank Account ):**
**Chase Bank**
**Routing Number: 044000037**
**Account Number: 789304011**

**3ኛ/ አዲሱ ኢሜል አድራሻችን ( Our New E-mail Address ):**
**ethiopianborder@yahoo.com**

**የድንበር ኮሚቴው የPaypal Account በAbbaymedia.com ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።**

**ውድ ወገኖቻችን ሆይ! ይህን ለውጥ በማገናዘብ ለሃገራችን ሕልውና እያደረግን ያለውን ከፍተኛ ሥራ በትጋት እንድንቀጥል የተለመደውን ሃገራዊ ጥሪ እናቀርባለን።**

**የሃገራችን ዳር ድንበር በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!**
**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

**የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**